የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF LABOUR AND SOCIAL AFFAIRS - ETHIOPIA

# የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## አስመልክቶ የቀረበ አጭር ማብራሪያ

2014ዓ.ም

አዲስ አበባ

**የማሻሻያው አስፈላጊነት**

የሙያ ደህንነት፣ ጤንነትና የሥራ አካባቢ አገልግሎት ኢኮኖሚያዊ፣ማህበራዊና ሰብዓዊ ገፅታ ያለው ሲሆን በሥራ ላይ ለተሰማራው አምራች ኃይል ምቹ የሥራ አካባቢ በመፍጠር፣ ንብረትን ከድንገተኛ አደጋ በማጠበቅ፤ ምርታማነትን በሚጨምር፤የሥራ ቅልጥፍና እና ጥራትን በማሳደግ በገቢያ ወስጥ ተወዳዳሪና ተሸላሚ እንዲሆን በማስቻል ሠራተኛወኝ ከኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካላዊ ጉዳት ይከላከላል፤ ደህንነቱንና ጤንነቱን ያረጋግጣል፡፡ በሥራ ቦታዎች እና አካባቢዎች ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ፣ ደህንነቱና ጤንነቱ የተጠበቀ ምርታማና ወጤታማ አምራች ኃይል ለመፍጠር ከሚያስችሉ እርምጃዎች ወይም ቅድመ ሁኔታዎች መካከል በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም አንቀፅ 92/2 በተቀመጠው መሠረት በድርጅቶች እና ኢንዱስትሪዎች የአደጋ ተከላካይ ሠራተኛ /ሴፍቲ ኦፊሰር/ መመደብ እና የሙያ ደኅንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ ማቋቋም ወሳኝ ነው፡፡ ይህም የሥራ ቦታዎችና አካባቢዎች በሠራተኞች ደህንነትና ጤንነት ላይ አደጋ የሚያስከትሉ እና ምቹ (Decent Work) መሆናቸወን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 ዓ.ም ተሻሽሎ በአዲሱ የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም በመተካቱ ምክንያት መመሪያወን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡ ስለሆነም በተሻሻለው የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 ዓ.ም. መሠረት ከመስከረም 1998 ዓ/ም ጀምሮ በስራ ላይ የነበረው ‵′የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ አቋቋምን ለመወሰን′′ የወጣ መመሪያ በመከለስና አስፈላጊ ማሻሻያ በማድረግ ተፈፃሚ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ ይህ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

**የረቂቅ ማሻሻያው የዝግጅት ሂደት**

ከክልል እና ከተማ አስተዳደር የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ/ኤጀንሲ/ጽ/ቤት፣ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከጤና ሳይንስ ኮሌጅ፣ ከሴቶች ወጣቶችና ህፃናት ሚኒስቴር፣ ከጠቅላይ አቃቤ ሕግ፣ ከአሰሪ ፌደሬሽኖች ኮንፌደሬሽን፣ ከኢትዮጵያ ሰራተኛ ማህበራት ኮንፌደሬሽን እንዲሁም ከተለያዩ ባለድርሻ አካለት እና ግለሰቦች ጋር በጋራና በተናጠል በተካሄዱ የወይይት መድረኮች በተገኙ ግብዓቶች መመሪያወኝ የማሻሻል ስራ ተከናወኗል ፡፡**በመጨረሻም ለሚኒስትር መ/ቤቱ ማኔጅመንት አባላት ቀርቦ በተደረገ ውይይት ዳብሮ እንዲፀድቅ ተደርጓል ፡፡**

**የረቂቅ መመሪያው ማሻሻያ የተደረገባቸው ዝርዝር አንቀፆች ይዘት**

ረቂቅ ማሻሻያው 27 አንቀፆችን የያዘ ሲሆን በአንቀፅ 2 አጭር ርዕስ በሚል የተቀመጠው ማስተካካያ የተደረገበት ሲሆን ይኸወም የቀድሞ ርዕስ ‶የሙያ ደህንነትና ጤንነት ተከታታይ ኮሚቴ አቋቋምን ለመወሰን

የወጣ መመሪያ" የሚል ሲሆን አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 171/1(ኀ) ላይ በተገለፀበት አግባብ መቀመጡ ተገቢ ሆኖ ስለተገኘ "የሙያ ደህንነትና ጤንነት ኮሚቴ ስለሚቋቋምበት ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ" በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ አንቀፅ 3 ትርጉም ቀደም ሲል በአዋጅ 1156/2011 አንቀፅ 2 በትርጉም ክፍል ላይ የተተረጎሙ ቃላትን መመሪያ ላይ መድገም አስፈላጊ ባለመሆኑ እዲወጡ ተደርጎ በመመሪያው ላይ የተገለፁ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ቃላት ብቻ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ አንቀፅ 4 የተፈጻሚነት ወሰን በሚለው ወስጥ በቀድሞ መመሪያ በቅርንጫፍ ድርጅቶች ሊኖር ስለሚገባው የሴፍቲ ኮሚቴ አደረጃጀት ምንም አይነት ምላሽ የማይሰጥ በመሆኑ ከድርጅቶች ተቋማዊ አደረጃጀትና የሥራ ባህሪ አኳያ ተጠሪነታቸው ለዋናው ድርጅት ሆኖ በቅርንጫፍ ደረጃ ተመሳሳይ ተልዕኮ ለሚፈፅም የተቋቋሙ ድርጅቶች ራሱን የቻለና ከዋናው የሙያ ደህንነትና ጤንነት ጋር በተጣጣመ ሚልኩ አደረጃጀት ሊፈጥሩ እንደሚችሉ የሚገልፅ ንኡስ አንቀፅ እንዲካተት ተደርጓል፡፡ አንቀፅ 5 የሙያ ደህንነትና ጤንነት ስለሚቋቋም በሚገልፅበት ስር የኮሚቴ አባላት ስብጥርም የቁጥር ማስተካካያ የተደረገበት ሲሆን በቀድሞ መመሪያ ላይ አሰሪ "የሠራተኞች ቁጥር ከ10-30 ሲሆን ከአሠሪው እና ከሠራተኞች ከእያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ተወካይ ይመርጣሉ" የሚል ሲሆን ሬንጁ ጠበዋል ማስፋት አለበት የሚል አስተያየት በመኖሩ በተደረገው ማሻሻያ ላይ የሌሎች አገራትን ልምድ በማየት ቁጥሩን ከ10-100 እንዲሆን የተደረገ ሲሆን የኮሚቴው አደረጃጀት ለሴቶች ተሳትፎ ትኩረት የሰጠ መሆን እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ አንቀፅ 6 የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ላይ ከአደጋ መከላከያ አላባሳት አጠቃቀም ክትትልና ቁጥጥር፣ ከሴቶች ጾታዊ ጥቃት መከላከል፣ከኮቪድ-19 ወረርሽኝን መከላከል አንፃር የተጨመሩ ተግባርና ኃላፊነቶች ሲኖሩ ይህንን ሚጨመር ያስፈለገበት ምክንያት አሠሪ ለደህንነት ማጠቢያ የሚያቀርበወን አልባሳት እና የሥራ መሣሪያ በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ ሚረጋገጥ ስላለበት፣በሥራ ቦታዎች በሴት ሠራተኞች ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ወሲባዊ ትንኮሳዎችን ወይም ጥቃቶችን ከመድረሳቸው በፊት አስቀድሞ ለመከላከል የሚያስችሉ የግንዛቤ ስራዎች በኮሚቴው እና ለዚሁ ዓላማ በተደራጁ ክፍሎች አማካይነት ማስራት ስለሚኖርበት እንዲሁም የኮቪድ-19 ወረርሽኝን እና በሀገር አቀፍና በዓለማቀፍ ደረጃ የሚከሰቱ ማናቸውንም ወረርሽኞችን በስራ ቦታ ከመካላከል ረገድ ከሌሎች አግባብ ካላቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ማስራት ስላለበት ሁኔታ ተደንግጓል፡፡

አንቀፅ 7 የኮሚቴ አባላት አመራረጥ የሚል ሲሆን የቀድሞ ላይ "በማህበር የተደራጁ ሠራተኞች በማህበራቸው አማካይነት አባላትን ይመርጣሉ፤ በማህበር ያልተደራጁ ሠራተኞች በድምፅ ብልጫ አባላት ይመርጣሉ" የሚል ሲሆን አንቀፁን የተብራራ ከማድረግ አንፃር በተሻሻለው መመሪያ ላይ ራሳቸውን የቻሉ ንዑስ አንቀፆች እንዲሆኑ በማድረግ "በማህበር የተደራጁ ሠራተኞች በማህበራቸው አማካይነት አባላትን ይመርጣሉ" የሚለወን በአንድ ንዑስ አንቀፅ "በማህበራ ያልተደራጁ ሠራተኞች ያሉበት ድርጅት አባላቱ በቀጥታ በሠራተኞቹ ይመርጣሉ" የሚለው በሌላ ንዑስ አንቀፅ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በቀድሞ መመሪያ በዚሁ አንቀፅ በንኡስ አንቀፅ ደረጃ ተገልፆ የነበረው የኮሚቴ አባላት የሥራ ዘመን የሚለው በተሻሻለው መመሪያ የበለጠ ግልፅ እንዲሆንና ጎላ ብሎ እንዲታይ ራሱን ችሎ አንቀፅ 8 ሆኖ እንዲቀመጥ

ተደርጓል፡፡ አንቀፅ 8 የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን በሚለው ስር በንዑስ አንቀፅ 3 ላይ የምርጫውን ጊዜውን ያልጨረሰ የኮሚቴ አባል በሌላ መተካት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኮሚቴው ከተተኪዎች መካከል አባል እንዲሆን በድምፅ ብልጫ ይመርጣሉ የሚል አዲስ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

አንቀፅ 9 የኮሚቴ አባላት ስልጠና በሚለው ስር ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ በቀድሞ መመሪያ ላይ እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል የኮሚቴው አባል ሆኖ በተመረጠ በስድስት ወር ጊዜ ወስጥ መሠረታዊ የሙያ ደህንነትና ጤንነት ስልጠና እንዲያገኝ መደረግ አለበት ይል የነበር እያንዳንዱ የኮሚቴ አባል ስልጠና ማግኘት ያለበት የኮሚቴ አባል ሆኖ በተመረጠ በሁለት ወር ጊዜ ወስጥ እንዲሆን በሚል እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

አንቀፀ 10 ስለ ኮሚቴው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ አመራረጥ የሚገልፅ ሲሆን በዚህም ከአሰሪና ሰራተኛ ከሚወክሉ ኮሚቴ አባላት ወስጥ ኮሚቴ በሚያወጣው የአሰራር ስርዓት መሠረት በየአመቱ በየተራ እየተቀያየሩ ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ሆነው የሚያገለግሉ አባል እንደሚመረጡ ተደንግጓል፡፡ አንቀፅ 12 ኮሚቴው ወሳኔዎችን የሚወስነው በድምፅ ብልጫ በመሆኑ እኩል ድምፅ በሆነ ግዜ ሰብሳቢው ያለበት የወሳኔ ሀሳብ ሆኖ እንደሚያዝ ተመላክቷል፡፡

አንቀፅ 14 የኮሚቴው ሰብሳቢ ተግባርና ሀላፊነት በሚለው ስር በኮሚቴው በኩል የሚቀመጡ የማሻሻያ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ መደረግ አለመደረጋቸውን ይከታተላል እንዲሁም አሠሪወና ኮሚቴው ወቅታዊ የጋራ የምክክር መድረኮች እንዲኖራቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል የሚሉ አዲስ ተግባርና ኃላፊነቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ የኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ ተግባርና ሀላፊነት የሚደነግግ አዲስ አንቀፅ 15 ተጨምሯል፡፡

አንቀፅ 18 የአሠሪ ኃላፊነቶች በሚለው ስር በሥራ ቦታዎች ለሴቶች፣ ወጣት ሠራተኞች፣ ኤች.አይ.ቪ ቫይረስ በደማቸው ያለባቸው ወገኖችና አካል ጉዳተኞች ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን እገዛ እና ድጋፍ እንዲሰጥ ያደርጋል እንዲሁም ሴት ሠራተኞች በሥራ ቦታ ከሚደርስባቸው ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት ለመጠበቅ የሚያስችሉ አሠራሮች እንዲዘረጉ ተግባራዊ እንዲደረጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል የሚሉ አዳዲስ ተግባርና ኃላፊነቶች እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

አንቀፅ 19 የሠራተኞች ኃላፊነት በሚለው ስር ሴት ሠራተኞች በሥራ ቦታ ከሚደርስባቸው ጾታዊ ትንኮሳ ወይም ጥቃት እንዲጠበቁ ጥረት ማድረግ የሚል አዲስ ተግባርና ኃላፊነት እንዲካተት ተደርጓል፡፡

አንቀፅ 20 ስለመመዝገብ በሚለው ስር ኮሚቴው በሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ባለው ባለሥልጣን ተመዝግቦ በየአመቱ የሚታደስ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጠው እንዲሁም ኮሚቴው የአባላት ለወጥ ሲያደርግ ሁኔታውን ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ማሳወቅ ያለበት ስለመሆኑ ተቀምጧል ፡፡ አንቀፅ 21 ስለ ሪፖርት አቀራረብ በሚለው ስር ኮሚቴው በድርጅቱ የተከሰቱ አደጋዎችና የደረሱ ጉዳቶች መኖር አለመኖራቸውን የሚገልፅ የአደጋ ሪፖርት በወሩ የመጨረሻ ሳምንት ላይ ለአሠሪው እና ለሚኒስቴሩ ወይም አግባብ ላለው ባለስልጣን ሪፖርት ያቀርባል የሚል ተግባር እንዲካተት ተደርጓል፡፡

**በመጨረሻም** ከአንቀፅ 21 እስከ 27 ያሉት ስለ ተጠሪነት፣ መመሪያውን ለማስፈጸም የማንኛውም አካል የመተባበር ግዴታን፣ መመሪያውን ስለማሻሻል፣ የተሻረ መመሪያ፣ መመሪያውን የተላለፈ አካል ላይ ስለተቀማጠ ቅጣት እና መመሪያው ስለሚፀናበት ጊዜ የሚደነግጉ አንቀፆችን ያካተተ ሆኖ ተደንግጓል፡፡